Gəʿəz I /ግዕዝ አሐዱ/

መግቢያ

ይህ ኮርስ ለግዕዝ ትምህርት መሠረታዊ የሆኑቱን ነገሮች ማጥናትን ይመለከታል። የሚጠኑትም ነገሮች የግዕዝ ተውላጠ ስሞች ፣ ቅጽሎች ፣ የነባርና የዘርእ ቃላት ፣ ነጠላ ግሦች ፣ የተመረጡ የደቂቅ ዕርባታዎች ፣ የግሥ ዕርባታዎችና የግዕዝ ቁጥሮች ናቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ የተለያዩ ኮርሶችን ከመማራቸው በፊት ቃላቱንና ተርጉማቸውን ማጥናት ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር በመሆኑ ነው። ስለዚህ ይህ የማስተማሪያ መጽሐፍ ከላይ የተገለጹትን አርእስተ ትምህርት መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል።

1. የተውላጠ ስሞች አመዳደብ

ተውላጠ ስም/ስሞች/መራሕያን/ ስምን ተክተው የአረፍተ ነገር ባለቤት እየሆኑ ይገባሉ። እነርሱም በሦስት አይነት መደብ ተበድበው ሊጠኑ ይችላሉ።

አንደኛው ምድብ

አንደኛው የምድብ አይነት ሁለት ክፍሎችን የሚይዝ ሲሆን ባንድ በኩል የነጠላ ቁጥሮች ተውላጠ ስሞችን (ውእቱ ፣ ይእቲ ፣ አንተ ፣ አንቲና አነ) በሌላ በኩል የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞችን (ውእቶሙ ፣ አንትሙ ፣ ውእቶን ፣ አንትንና ንሕነ) በማስቀመጥ ይመድባል።

ሁለተኛ ምድብ

ሁለተኛው የምድብ አይነት ተውላጠ ስሞችን በሦስት የሚከፍል አመዳደብ ሲሆን አንደኛ መደብን (ሪ ፣ ንሕነ) ፤ ሁለተኛ መደብን (አንተ ፣ አንቲ ፣ አንትሙ ፣ አንትን)ና ሦስተኛ መደብን (ውእቱ ፣ ይእቲ ፣ ውእቶሙ ፣ ውእቶን) ይይዛል።

ሦስተኛ ምድብ

ሦስተኛውም አመዳደብ ዐሥሩን/ዐሥራ ሁለቱን/ ተውላጠ ስሞች/መራሕያን በእሩቅና በቅርብ ያታዎች የሚመድብ ይሆናል። በዚህ ምድብ የሚገኙት ተውላጠ ስሞችም ውእቱ ፣ አንተ ፣ ይእቲ ፣ አንቲ ፣ ውእቶሙ ፣ አንትሙ ፣ ውእቶን ፣ አንትን ፣ አነና ንሕነ ናቸው። ይህ ሦስተኛው አመዳደብ በአብነት (ግዕዝ) ትምህርት ቤት የተለመደ ሲሆን በአንደኛውና በሁለተኛው የተገለጸው አመዳደብ የዘመናዊ ትምህርት ቤት አመዳደብ ነው።

1.2. ያሥሩ ተውላጠ ስሞች/መራሕያን ትርጉሞች

ውእቱ = ነው	ውእቶሙ = ናቸው	አነ = ነኝ
አንተ = ነህ	አንትሙ = ናችሁ	ንሕነ = ነን
አንቲ = ነሽ	ውእቶን = ናቸው	
ይእቲ = ናት	አንትን = ናችሁ	

እነዚህም ተውላጠ ስሞች የአረፍተ ነገር ባለቤቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ የአረፍተ ነገር ማሠሪያ ግሦች ወይም አንቀጾች ይሆናሉ።

ውእቱ ውእቱ = እርሱ ነው

አንተ ውእቱ = አንተ ነህ

ይእቲ ይእቲ = እርሷ ናት

አንቲ ውእቱ = አንች ነሽ

ውእቶሙ ውእቶሙ = እነርሱ ናቸው።

አንትሙ ውእቱ = እናንተ ናችሁ

ውእቶን ውእቱ = እነርሱ ናቸው

አንትን ውእቱ = እናንተ ናችሁ

አነ ውእቱ = እኔ ነኝ

ንሕነ ውእቱ = እኛ ነን

ምሳሌ

አነ ውእቱ አቡሁ ለዝናም = የዝናም አባቱ እኔ ነኝ።

አንትሙ ውእቱ ንዋይ ኅሩይ = እናንተ የተመረጠ ዕቃ ናችሁ።

ውእቱ ብእሲ አልቦ ውሰተ ዝ ቤት ያ ሰው በዚህ ቤት ውስጥ የለም።

ከዚህ በላይ የተከለጹት ያሥሩ መራሕያን ማሠሪያ አንቀጽ መሆን በውእቱ ብቻ ይተረጎማሉ።

1.2. ቅጽል የሚሆኑ ተውላጠ ስሞች

1.2.1. የባለቤት ቅጽሎችና ትርጉማቸው

ዝ፣ዝንቱ = ይህ

ዛ፣ዛቲ = ይህች

እሉ፣እሎንቱ = እሊያ/እነዚያ

እላ፣እላንቱ፣እሎን = እሊያ

ዝኩ፣ዝስኩ፣ዝክቱ = ያ

እንትኩ = ያች

እንታክቲ = ያች

እልክቱ = እሊያ

እልኮን = እሊያ

እልክቶን = እሊያ

ምሳሌ ፩

1. ዝንቱ ካህን አእመረ ምስጢረ = ያ ካህን ምስጢርን ዐወቀ
1. አንተ ካህን አእመርከ ምስጢረ = አንተ ካህን ምስጢርን አወቅህ
2. እሉ እደው አእመሩ ነጊደ = እሊያ ኅበዞች መነገድን ዐወቁ
3. አንትሙ እደው አእመርክሙ ሐኒጸ = እናንተ ኅበዞች ቤት ማነጽን ዐወቃችሁ
4. ዛቲ ብእሲት አእመረት ፈትለ = ያች ሴት ፈትልን ዐወቀች
5. አንቲ ብእሲት አእመርኪ ፈትለ = አንች ሴት ፈትልን ዐወቀሽ
6. እላ አንስት አእመራ ፈትለ = እሊያ ሴቶች ፈትልን ዐወቁ

7. አንትን አንስት አእመርክን ፈትለ = አናንተ ሴቶች ፈትልን ዐወቃችሁ

8. አነ ካህን አእመርኩ ምሥጢረ = እኔ ካህን ምሥጢርን አወቅሁ

9. አነ ብእሲት አእመርኩ ፈትለ = እኔ ሴት ፈትልን ዐወቅሁ

10. ንሕነ ካህናት አእመርነ ምሥጢረ = እኛ ካህናት ምሥጢርን ዐወቅን

11.ንሕነ አንስት አእመርነ ፈትለ = እኛ ሴቶች ፈትልን ዐወቅን

ምሳሌ ፪

ዝ/ዝንቱ ረድእ ተአጋሚ ውእቱ = ይህ ተማሪ ታጋሽ ነው።

ዛ/ዛቲ ወለት ጠባብ ይእቲ = ይህች ልጅ ብልሃተኛ ናት።

እሉ/እሎን ሐዋርያት ክቡራን ውእቶሙ = እነዚያ ሐዋርያት የተከበሩ ናቸው።

ዝኩ/ዝስኩ/ዝክቱ ሚካኤል መልአከ ምሕረት ውእቱ = ያ ሚካኤል የይቅርታ መልአክ ነው።

እንትኩ/እንታክቲ እም መፍቀሪተ ወልዳ ይእቲ = ያች እናት ልጇን ወዳጅ ናት።

እላ/እሎንቱ/እላንቱ/እላ/እልኩ/እልክቱ/እልኮን/እልክቶን ደናጋል መሓርያት ነዮን = እሊያ ደናግል ይቅር ባዮች ናቸው።

1.2.2 የተሳቢ ቅጽሎች/ገላጭና ትርጉማቸው

ዘ፣ዘንተ = ይህን	ዝኩ = ያን	እልኩ = እሊያን
ዛ፣ዛተ = ይህችን	ዝስኩ = ያን	ዝክተ = ያን
እሎንተ = እሊያን	እልኮን = እሊያን	እንትኩ = ያችን
እላ፣እላንተ = እሊያን	እልክቶን = እሊያን	እንታክተ = ያችን

2. ዘርእና ነባር ቃላት

በዚህ ርእስ ከተለያዩ ግሦች የሚወጡትን ቃላትና ነባር ስሞችን ከነትርጉማቸው ማጥናት ይመለከታል።

2.1. ዘርእ ቃላት

ዘርእ ማለት የተለያየ ቅርፅ በመያዝ ከግሥ የሚወጣ ቃል ሲሆን እንደሚከተሰው ይቀርባል።

ሀ/ሐ

ለውህ = ብራና

ላህ = ለቅሶ

ብጎባኄ = ክርፋት

መድበል = መከማቻ

መተንብል = አማላጅ

ምስያህ = መውቀጫ

መርኖ = መክፍቻ

ምጽባሕ = ወጭት

ሠራሔ = ብርሃን

በራህ = እራሰበራ

አምኃ = እጅ መንሻ

ለ

ሉዓሌ = ከፍታ

ሐቃል = ብርቱ

ሐቅል = በረሃ

መስእል = ለማኝ/አማጣኝ

መተንብል = ለማኝ/ጸሎተኛ

መዋዕል = ዘመን

መድበል = መከማቻ

ሣህል = ይቅርታ

ሰገል = ዕውቀት

ብሂል = ማለት

ቀበላ = መቀበል

ቀጸላ = ቆብ/ጥምጥም

ኒል = ሰማያዊ ቀለም

ኀያል = ብርቱ

ገይል = በርታት

አዛል = ብርቱ

እክል = እህል

ወዓሊ = ሠራተኛ/ሎሌ

ድንጋሌ = መጠበቅ

ድንግል = ጥብቅ

መ

ሐማሚ = ምቀኛ

ሐኪም = ወጌሻ

ሕመሜ = ምቀኝነት

መስተሳልም = አፍቃሪ

ዐቅም = ልክ

ማሕመሚ = አሳማሚ

ማሕመም = ምጥ

ማኅተም = ቅርፅ

ምሥያም = ሳጥን

ምስያም = አገልግል

ሱላሜ = ፍቅር

ቃውም = አለቃ/ተከራካሪ

ንዋም = እንቅልፍ

ሰ

ሠሉስ = ሶስተኛ/ማክሰኞ

ሣልስ = ሦስተኛ

መያሲ = አሳላፊ

ሰንኮሪስ = አስተማሪ

ርእስ = ራስ/አለቃ

ሮስ = ልጅ

ባእስ = ጠብ

ንኡስ = ትንሽ

ነኣስ = ታናሽ (ለሴት)

ረ

ሁባሬ = አንድነት

ኀሬ = መመረጥ

ሕዋር = ወልወል/ወለል

መንክር = ድንቅ

መዘክር = አሳሳቢ

ምሕዋር = መሄጃ

በ

ሐሊብ = ወተት

መስተሐብብ = አንጎራጓሪ

መክብብ = ሹም

ማኅፀብ = መታጠቢያ

ምሥራብ = መጠጫ

ቀ

ምሥራቅ = መውጫ

ምውቅ = የሞቀ/ሙቅ

ሠርቅ = ንጋት/መቫቻ

ተ

ሕለት = ዘንግ

ሕይወት = መኖር

ጎብስት = እንጀራ/ዳቦ

ህድአት = ፀጥታ

መሐዛት = ጎልማሶች

መሀይምን = አማኝ

መሐደምት = ተረት

መላህቅት = ሽማግሌዎች/አለቆች

መላእክት = አለቆች

መስቴ = መጠጫ

መሌሊት = ብልት

መምህርት = ሴት መም(ህ/ር

ምፅማር = ባልና ሚስት

ቀመር = ቁጥር/ዋልታ

ኄር = ቸር

ምርካብ = ደመወዝ

ምንዳቤ = ችግር

ዕፁብ = ድንቅ

ዕፁብ = ጭንቅ

ክታብ = ደብዳቤ

ረቅ = ብራና

ነዳቂ = አናጺ

ንድቅ = ቤት/ሕንፃ

መሥገርት = ወጥመድ

መባሕት = ሥልጣን

መንሱት =ጥፋት

መንጠላዕት = መጋረጃ

ወዐለት = ሎሌዎች/የቤትአሸከሮች

መክፈልት = ድርሻ/እድል ፈንታ

መጽሔት = መስታውት

ሚሕሌት = ዝማሬ

ማኅቶት = መብራት

ማኅፀንት = አደራ

ማዕሌት = ክፉ ምክር

ማዕሌት = ክህደት/መሸፈት

ገፃር = ጨኸት

ፍካሬ = ትርጉም

ይባቤ = እልልታ

ጥበብ = ብልሃት

ጥብ = ጡት

ዑቅ = ዕወቅ/ጠብ

ማዕዶት = መሻገሪያ

ማዕሠርት = ወጥመድ

ምሴት = ምሽት

ረበናት = መምህራን

ተምኔት = ምኞት

ተናብልት = መልእክተኞች

ተውኔት = ጨዋታ

ኩነት = ሁኔታ

ኖኅት = በር/ደጃፍ

ኂሩት = ቸርነት

ወልታ = ጋሻ

ጥብዐት = መጨከን/ጭካኔ

ጥውየት = ጠማምነት

ዖታ = ወገን

ነ

ሕርትምና = ጉስቁልና

ሊጠን = ልመና/ጸሎት

ልሳን = ምላስ/አንደበት/ቋንቋ

መሐና = እጅ መንሻ

መካን = ያልወለደች

ፍልጣን = መፋታት

መካን = ቦታ/መኖሪያ

ሚን = ተንኮል

ምዕቅብና = አደራ

ምዕዳን = ምክር

ሥን = ውበት/ደምግባት

ሰብአ ዐይን = ጎብኚች

ቀኖና = ሥርዐት

ኪን = ጥበብ

አ/ዐ

ላዕላዕ = ለምባዳ/ድዳ

መልክአ = መልክ

መርዓ = ግቢ፣ ጋብቻ/ሠርግ

መናቅዕ = ቁርችምጭት/ተረከዝ

መጥቅዕ = ደወል

መ·ባእ = መግቢያ

መ·ፃእ = መውጫ

ምጽናዕ = መሠረት

ሳብዕ = ሰባተኛ

ክልኤ = ሁለት

ጽዋኤ = መጠራት

ፍግዕ = ደስታ

ከ

ሀውክ = ሁከት

ሀከክ = ክርክር

ብርክ = ጉልበት

ምዑክ = ቁጡ

ዐርክ = ወዳጅ

ዋካ = ብርሃን

ወ

ህላዌ = ኑሮ/አኗኗር

ለባዊ = አስተዋይ

ለብሶ = ማስተዋል

ዐላዊ = ከዳተኛ

ቅድው = ያማረ

ብጽው = እንቅልፍ

መዜንው = ወሬ ነጋሪ

መደልው = ግብዝ

ሰዋስው = መሰላል

ተቃሕሶ = ፍክክር

ተጓሕልሶ = ሽሙጥ

አዕላዊ = ተርጓሚ

ከዋው = ቀልጠፋ

ኬንያዊ = ብልሃተኛ

ዘምዎ = ማመንዘር

ዜናዊ = ወሬ ነጋሪ

ግጽው ፊት = ለፊት ያለ

ጽማቄ = ቀስታ/ድንቁርና

ጽምው = ጭምት/የረጋ

ዘ

ሐዋዝ = መልካም

መዓዛ = ሽቱ

ምሁዝ = ተጫዋች

ምዑዝ = ጣፋጭ

ቤዛ = መድኃኒት/ስለ/ ፈንታ

አዚዝ = ጽኑ

አግዓዚ = ነፃ የወጣ/ነፃ የሚያወጣ

ጋእዝ/ጋዕዝ = ክርክር

የ

ሀካይ = ሰነፍ

ሊሉይ = ልዩ

ላህይ = ደም ግባት

ተናሕዮ = ራስን መግለጽ/መናዘዝ

ኖትያ = ዋናተኛ

ኬንያ = ብልፃተኛ

ጠዋይ = ጠማማ

ልሁይ = መልከ መልካም

መራእይ = መነጽር

ሠናይ = መልካም

ዕቡይ = ትቢተኛ

ጉሕልያ = ሽሙጥ

ደ

መራድ = ወራሪ/ተራማጅ

መንገድ = መንገድ

ሙራድ = መውረጃ

ሠሌዳ = ብራና/ነጭ ቦርድ

ረዋዲ = ጠላት

ረዓድ = እንቅጥቅጥ

ባዕድ = ልዩ

ተዋሕዶ = መዋሐድ

ተዋርዶ = መዋረድ

ተአንግዶ = እንግድነት

ነባድ = ወገን

ነጋዲ = ነጋዴ

ነግድ = እንግዳ

እንግዳ = እንግዳ/ደረት

ክቡድ = ከባድ

ዐብድ = ሰነፍ

ዐምድ = ምሰሶ

ዐዋዲ = አዋጅ ነጋሪ

ዐውድ = አደባባይ

ዐውድ = ዙሪያ

ዐውድ = አውድማ

ፀዓዳ = ነጭ

ገ

ሕግ = ሥርዐት/ድንጋጌ
ንትጋ = ጎደሎ
ድንጋግ = ወሰን
መንሰግ = መቆለፊያ
ጎዳግ = የመጽሐፍ ጠርዝ
ጸዋግ = ክፉ
ምዕራግ = መሰላል
እንግልጋ = ስብስብ
ሠርጉ = ጌጥ
ዘውግ = ወገን

ጠ

ሐያጢ = ሸንጋይ
ሜጥ = ዋጋ
ስባጥ = ጉርሻ
መሠጥ = ነጣቂዎች
ሰሐጢ = ቆንጣጭ/አጫሪ
ቀበያውባጢ = ቀላዋጭ
ምሥያጥ = ገበያ
ሰውጥ = አለንጋ
ተውላጥ = ለውጥ

ጸ

ህጼ = ማጫ
ማህረፅ = ወፍጮ
ነፈርዓጽ = ደስታ
ሐሪጽ = ዱቄት
ማዕያ = መዝጊያ
ፋጻ = ፉጨት
መላፂ = ምላጭ
ሠርፅ = ቡቃያ
መስተዳጉጽ = አነካኪ/አጣዩ
ተግሣፅ = ቁጣ/ዘለፋ

ፈ

ሐፍ = ወዝ/ላበት
መጽሐፍ = ወግ
አጽፍ = ልብስ/ዳባ
ሐዳፍ = ቀዛፊ/መምህር
መጽሐፍ = ዕውቀት
እልፍ = ቁጥር
መንጸፍ = ምንጣፍ
ምዕራፍ = ማረፊያ/ማሳረፊያ
ዝሉፍ = አውታታ
መጽሐፍ = መጽሐፍ
ሱታፌ = አንድነት
መጽሐፍ = መምህር
ተስፋ = አለኝታ/አመኔታ

ተስእሎት አሐዱ

ከዚህ በላይ የተገለጹትን ቃላት ከዚህ በታች ከ1-10 በቀረቡት ቃላት መድበህ አሳይ/ዪ

1) የምስጋና ቃላት.....
2) የሥራ ቃላት.....
3) የዕውቀት ቃላት....

4) የቦታ ቃላት.....
5) የአዝርእት ቃላት....
6) የአትክልት ቃላት.....
7) የዕፀዋት ቃላት.....
8) የሹመት ቃላት....
9) የቁሳቁስ ስያሜዎች...
10) የአልባሳትና የመዓድን ቃላት....

2.2. ነባር ቃላት

ነባር ማለት የቆየ/ያለና የሚኖር ማለት ሲሆን ከግሥ የማይወጣ ቃል ወይም ግሥነት የሌለው ቃል ነው። ይህም የሰውና የእንስሳ አካላትን እንሰይምበታለን። እንዲሁም መላእክትን ፣ ዕፀዋትን ፣ የውሃ አካላትንና የዓለም ሀገሮችን የምንሰይምበት ቃል ነው።

2.2.1. ከሀ -ፐ የተመረጡ ነባር ቃላት

ሀ/ሐ

በሐ = እንዴት ዋልህ
ለሊሁ = እርሱ ቅሉ
ምስሌሁ = ከእርሱ ጋር
ርሔ = ሽቱ
ብእሲሁ = ሰውየው
ናሁ = እነሆ
እሊአሁ = የርሱ
ሰላምሂ = ደጀሰላም
ሶቤሃ = ያንጊዜ
ቁፋሂ = ቅኔ ማሕሌት
ተዳሂ = ቤተ ልሔም
ጎቤሁ = ወደእርሱ
አካሂ = ጥገት
አሜሃ = ያንጊዜ
አፈ ጽባሕ = ንጋት
ኵሰሄ = ሁል ጊዜ
አንቆቅሆ = እንቁላል
አፍትሖ = ሹም
ኦሆ = እሺ
ጽርሐ = አዳራሽ

ለ

ሄላ = ምንጭ
ለለ = በየ
መንዲል = መሐረም
መንገለ = ወደ
ማዮባሊ = ዋስ
ምስለ = ጋራ
ሠረገላ = ጋሪ/መኪና
ስንዳሌ = ስንዴ
አላ = እንጂ
እለ = የ/እነ
እንበለ = ያለ
እሉ = እሊያ
ከዋላ = ኋላ
ዕብላ = ጨረቃ
አሌ = ወዮ
አውል = ጤዛ
አውሎ = ብርቱ ነፋስ
ወይሌ = ለቅሶ
ደወል = ሰበካ/አውራጃ
ገርዳሊ = ዳኛ
ጎል = በረት

ጠቃሊ = አመፀኛ

ጼተሎ = ጉሽ ጠጅ

መ

ቅድመ = ፊት

አመ = ጊዜ

አበደም = ደመኛ

እብነ ሐኪም = ልጅ

አዲም = ቀበቶ

አድያም = ዙርያ

እም = እናት

ዮም = ዛሬ

ጸጋም = ግራ

ፍጽም = ግንባር

ፋእም = ጉርሻ

ረ

ሐመር = መርከብ

ሐራ = ጨዋ

ሕምር = እንሶስላ

ሕብር = ቀለም

ሕንብርብሬ = ዝንጉርጉር

ሐጹር = አጥር

መብራ = አላማ (የቆመ ካገር) = ጌር

እንዚራ = በገና

ኮራ = ጽዋ/የቆመ ውሃ

ጌራ = ራስቁር

ግሙራ = ፊጽሞ

ሰ

ሐዊሳ = እንዴት ዋልህ

ሠራውር = ሱሪ

ሣህር = መባቻ

ሦከር = በንኪር

ልጥር = አሥራሁለት ወቄት

ቀመር = ቁጥር/ዋለታ/ገበታ

መርስ = ፀጥታ

ማር = ሊቅ

መዓርዒር = ጥፍጥ

ዘትር = ምንጭ

ዘፈር = ዘርፍ

ምሕማስ = መዋኛ

ሰ = ግን፣ና፣ሳ፣ስ

ሶ = ጨዋታ

ሶሶ = ዘፈን

ኤጲሞስ = ቀሚስ

ቃስ = ቀሚስ

ቆሞስ = የኤጲስቆጶስ መጋቢ

ጳጦስ = ጅባራ

ብናሴ = ጨረቃ

ዝሙር = ምስክር

ጠስ = ቅንድብ

ብእሲ = ሰው

ተስላስ = አዳራሽ

ተኬሳ = ትክሻ

አርማስ = መርከብ

አርማስቆስ = ግንብ

አክዮስ = ይገባዋል

ከኒሳ = ቤተ ክርስቲያን

ከርሥ = ሆድ

ፋሲልያሱ = ወዮ እኔ ልሙትል

ፊቃር = ቀሚስ

ቀ

ልሳን = ዘመርቅ አንቃር

ሕቀ = ጥቂት

ሕብረ ወርቅ = ወርቀዘቦ

በሕቁ = በጥቂቱ

ጣቃ = ጨለማ

ጥቃ = አጠገብ

በ

ሐቤ = የወታደር አለቃ

ሶቤ = ያን ጊዜ

አብ = አባት

ሕዝብ = ወገን

ራሕብ = ስፋት

ዘነብ = ጅራት

መርህብ = ሜዳ

አሳብ = ሙያተኛ

ሰብሳብ = ግቢ/ጋብቻ

አስብ = ደመወዝ

ተ

ህየንተ = ስለ/ፈንታ

ሐሴሜት = ድመት

ልቃሕት = ጉንጭ

ሐኔት = ሐሜት

ሕልቀት = ቀለበት

መላህቅት = ሌማት

ሐኖት = መሸታ ቤት

ላቲ = ለርሷ

ማዕሠርት = ወጥመድ

ሐይመት = ድንኳን

ሎቱ = ለእርሱ

መሳይምት = ሌማት/ቅርጫት

ቦቱ = በሱ

እንታክቲ = ያች

መራናት = መብራት

አንተ = አንተ

እዓለማውታ = ድህአደግ

መቅጹት ምንቸት

አያተ = እንደ

አበቅቴ = ትርፍ

መበለት = ባልቴት ሴት

ዕሤተ = ስለ/ዋጋ

ዛቲ = ይህች

መትሕት = ታች

ውስተ = በውስጥ

ዝንቱ = ይህ/ይኸው

መንቅዕት = ምንጭ

ውእተ = ያን

ዝክቱ = ያው

መንቅዕት = ወገብ/ብብት

ዘንተ = ይህን

ግብተ = ድንገት

መክሊት = ዐሥር ልጥር

ዛተ = ያችን

ውእቱ = ነው/ነህ/ንኝ

መዝራት = የእጅ መሐል አገዳ

ውእቱ = እርሱ

ብእሲት = ሴት

ሜላት = ነጭ ሐር

አሐቲ = አንዲት

አማዑት = አንጀት

ምት = ባል

አንቲ = አንቺ

ዐረፍት = ግድግዳ

ሣኒታ = ማግስት

አሎንቱ = እሊህ

አኪስት = ምንጮች

ኒቆታ = የሥዕል ቤት

እሙንቱ = እርሳቸው

እፎያዊት = እንዴት ያለች

ቅስት = ጥል

እማንቱ = እርሳቸው

ጸላዕት = ዋሻ

ባሕቱ = ነገር ግን

እስፍንቱ = ስንቱ

ነ

ለነ = ለኛ

ሕፅን = አጠገብ/ብብት

ሕርትምና = ጉስቁልና

መሐና = እጀመንሻ

መኑ = ማን ነው

ሚጣን = ምላስ

ምዕስብና = መፈታት

መጠነ = ያህል

ሰብአ ዐይን = ተመላካቾች/ጉበኞች

ስኒን = ሽቱ

ስን = ጥርስ

ከሙን = ተልባ

ከሚን = ፈጦ

ኪያነ = እኛን

ስፍን = ስንት

ቀቀኖ = ርኩም

ቅኔ = ግዛት/አገልግት

በይነ = ስለ

ብነ = አለን

ብለኔ = የመጣጠቢያ

ቦኑ = አለን/በውኑ/በውነቱ

ኑ = ቃለ ጥያቄ

ንሕነ = እኛ

አሐተኔ = አንድነት

አምጣነ = ና፣ያህል፣ስለ

ዛሕን = ፀጥታ

ደርከኖ = ብጫ ሐር

ገሪዛን = ግምጃ/ሻሽ

አነ = እኔ

አኮኑ = ና፣አይደለምን?

እምነ = ከ

እንበይነ = ስለ

ዐይነ = ስለ

ተወን = በልግ

ቴፃን = ጉልቻ

ናይን = የጣፈጠ

ናይን = ይቅር ባይ

አላቲኖን = ሰው የሆነ አምላክ

አሶርዮን = ገበያ

ጌና = በዓለ ልደት

ጠሊሳን = መጮናጸፊያ

ጸደና = የጋጃ ማር

አ

ረቡዑ = አራተኛ

ቍልዔ = ወዳጅ

ተስዑ = ዘጠነኛ

ነዓ = ና

ከርካዕ = ሎሚ

ገርድኡ = ዳኛ

አስትአ = እጅመንሻ

አኢ = ተመለስማ

እንዳኢ = እንጃ

እንግዳ = ደረት

ገባኢ = ሙያተኛ

ጥዕጡዕ = ምስጉን

ጉጉዓ = ችኮላ

ኦ = ወይ/ቃለ አክብሮ

ከ

ለከ = ላንተ

ምህርካ = ምርኮ

ሠርክ = ከሰዐት በኋላ

ብከ = ባንተ

ታዕካ = አዳራሽ

እልኩ = እነዚያ

እስኩ = እስኪ

እንትኩ = ያች

እስከ = ድረስ

እንከ = እንግዲህ

ወ

ማኅው = ብርሌ

ሰርዌ = ጉድፍ/አለቃ/ምሰሶ

ነዋ = እነሆ

አብያታዊ = ቤተ ሰብእ

እወ = አዎ/አዎን

አኬ = አ ሆይ

ኪያከ = አንተን

ዝንኩ = ያ

ዝኩ = ያ

ፔካ = መንበር/ወምበር

ፔርካ = ሽንብራ

አው = ወይም

አፈው = ሸቱ

እምሔው = አያት/እሚታ

እደው = ወንዶች

እድው = ደመኛ

ዐልዋ = ዘብ/ጥበቃ/ጤና ጥበቃ

ዕጓለ እመሕያው = ሰው/ባለአእምሮ

እፎያዊ = እንዴት ያለ

ፀራዊ = ጠላት

ዘ

በዘ = ስለ/እንደ

ማእዜ = መቼ

እምዘ = እንደ

እምይእዜ = ካእንግዲህ

ዘ = የ/በ/ወደ

ዘዘ = እየ

ከመዝ = እንዲህ

ይእዜ = ዛሬ

ጊዜ = ጊዜ

ጠረቤዛ = መንበር/ሰደቃ

የ

ህየ = ከዚያ

ርዴ = አራጣ

ሰይ = ወዮ

ብየ = አለኝ

ነያ = እነኚት

አልብየ = የለኝም

አርአያ = አምሳል

አስሐትያ = ውርጭ

አይ = ምን

ወይ = ወዮ

ዝየ = በዚህ/ከዚህ

ዬዬ = ወዮ

ዬ = ለቅሶ

ዴዴ = ደኻፍ

ፀደይ = ዘመነ በልግ

ደ

መከየድ = የእግር ጫማ

አነዳ = ዳባ

ኤፉድ = ዝናር/መታጠቂያ

እንግዳ = ደረት

ዐፀድ = የአትክልት ቦታ

እድ = እጅ

ዕድ = ወንድ

ዓዲ = ገና/ዳግመኛ

ከለሜዳ = ቀይ ግምጃ

ከብድ = ሆድ

ክሣድ = አንገት

ወእደ = ዘንድ

ዬዬ = ደጅ

ጋዳ እጅ =መንሻ

ፀዓዲዓድ = የነጭ ነጠብጣብ

ገ

ሐርጌ = ወይፈን/ጊደር

ሕገ = እንደ

ብእሴ = ውስጥ ነፍስ

እንጋ = ምንኛ

እንጋ = በውኑ

ንዋየ = ውስጥ ሆድ ዕቃ

ጎዳጥ = ጥቂት

አይኑግ = ጉትቻ

ዝንጓጌ = ሽሙጥ

ዮጊ = ወይ/አሁን

እንጋ = እንዴት

እንቁጥ = አፍንጫ

ጹግ = ክፋት/ቂም

ዮጊ = ዳግመኛ

ዮጊ = ያን ጊዜ/እስኪ

ጸ

ሁስጹ = አሸክት

ሐጾ = ዲያቆን

ምጕንጻ = ፍላፃ/ጦር

አጸሊጹ = ቤተ መቅደስ

ፀ

ለንጽ = መታጠቂያ

ልሳን ዘለጽሊጽ = አንቃር

ሐፅ = ጦር

ማህፄ = ምሳር

ሥሑፅ = ክፉ/ደፋር/ተሳዳቢ

ሥሑጽ = ጥልቅ ጥልቅ ባይ

አንቀጽ = በር/ደጃፍ

ዕፄ = ትል

ገጽ = ፊት

ፈ

ለዝሉፉ = አዘውትሮ

ለዝላፉ = ለዘወትር

ለፈ = ወዲህ/ወዲያ

ሐገፉ = ጋሻ

መትከፍ = ትክሻ

አፈ = ጊዜ

አሪፍ = አምና

አፍ = አፍ

አንፍ = አፍንጫ

እፎ = እንዴት/ምንኛ

እፎ = ምን

እፎ = ኧረግ

እፎ እፎ = እንዴት እንዴት

እልፍ = ወገን/ቁጥር/10,000

ገሪፍ = ወጥመድ

ጽንፍ = ዳር

የፐ

ለፓ = ሣር ካፓ = አጽፍ ፕፔ = ወዳጅ

ለምፓ = ቀንዲል አፐ = አርበኛ

ከረፐ = ገላ ኬፐ = አፍንጫ ኮፐ = ራስ

2. 2. 2. በሰው አካል ያሉ ነባር ስያሜዎች

ልሳን ዘመርቅ = ላንቃ ቀርነብ = ቅንድብ እድ = እጅ

ሐቋ = ዳሌ/ወገብ ቀኦይጽ = ጭን እግር = እግር

ሕጽን = ብብት/እቅፍ ብርክ = ጉልበት ከንፈር = ከንፈር

መልታሕት = ጉንጭ አምንትት = ጅማት ክሣድ = አንገት

መትከፍት = ትክሻ አንፍ = አፍንጫ ኩርናዕ = ክርን

መከየድ = ጫማ አጽባዕት = ጣት ዐይን = ዐይን

መዝራዕት = ግንድ አፍ = አፍ ዘባን = ጀርባ

ራሕ = እፍኝ እመት = ክንድ ድማህ = መሀል አናት

ርእስ = ራስ እንግዳ = ደረት ገቦ = ጎን

ስን = ጥረስ እዝን = ጆሮ ገጽ = ፊት

ተስእሎት ክልኤቱ

♣ ከዚህ በታች ከ1-7 የቀረቡትን ጥያቄዎች ተከቢውን ቃል በመጻፍ መልስ።

1. የአዝርእት ቃላት
   - ሀ.= ሰ.=
   - ለ.= ቀ.=
   - ሠ.= በ.=
   - ረ.= ተ.=
2. የ ዕፀዋት ቃላት
   1. = 6. =
   2. = 7. =
   3. = 8. =
   4. = 9. =
   5. = 10. =

3.የክብደት ቃላት
   1. = 3. =
   2. = 4. =

5. =

4. የግብር/የሥራ ቃላት

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =

5.የመጠን/ልክ ቃላት

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =

6.የጊዜ ቃላት

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =

7. የቤት ዕቃዎች ስያሜዎች

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =
6. =

ተስእሎት ሠለስቱ

♣ ከዚህ በታች ከ1-3 ለተጻፉት ቁጥሮች ተስማሚውን ቃል ጻፍ/ፊ።

1. የነገሮች ዮያሜ

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =

2. የመዓድን ቃላት

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =

3. ዖታ አመልካች ቃላት

1. =
2. =
3. =
4. =
5. =
7. =
8. =
9. =
10. =

ተስእሎት አርባዕቱ

♣ ከዚህ በታች የተገለጹትን ክፍት ቦታዎች ተገቢውን የአማርኛ ቃል ሙላ/ዪ።።

ምሳሌ፣

1) .....መውረጃ
2) ረዓድ .....
3) ረዋዲ .....
4) ዐውድ .....
5) ዐውድ .....
6) .....የአትክልት ቦታ
7) ..... ዝናር/መታጠቂያ
8) ከብድ .....
9) ..... አንገት
10)አነዳ .....
11).....ቀይ ግምጃ
12)ጋዳ .....
13).....ደጅ
14)ሐርጌ .....
15)ሕገ .....
16)አይኑግ .....
17).....በውኑ
18)ዝንጓጌ .....
19) ዮጊ .....
20)ዮጊ .....
21)ዮጊ .....
22).....ቂም
23)ጎዳጥ .....
24).....:ሆድ ዕቃ
25)እንቁጥ.....

ተስእሎት ኃምስቱ

♣ የሚከተሉትን የአማርኛ ቃላት በግዕዝ ቃላት ጻፍ/ፊ።።

ምሳሌ፣ ኩለሄ...ሁል ጊዜ ፣ አሆ...እሺ።።

1. እንዴት ዋልህ.....
2. ፀጥታ .....
3. ወደርሱ .....
4. እርሱ ቅሉ .....
5. ከእርሱ ጋር .....
6. ሰውየው .....
7. እነሆ .....
8. የርሱ .....
9. ደጀ ሰላም .....
10...ቅኔ ማሕሌት .....
11.ቤተ ልሔም .....
12.ጥገት .....

13.ያንጊዜ .....
14.ያንጊዜ .....
15.ሽቱ .....
16.ንጋት .....
17.እንቁላል .....
18.ሹም.....
19.አዳራሽ .....
20.እሺ .....

ተስእሎት ስድስቱ

♣ የሚከተሉትን የግዕዝ ቃላት ወደ አማርኛ መልስ።

ምሳሌ፣ አብ = አባት ፣ እም = እናት ፣ ወልድ = ልጅ ፣

1) ለነ =
2) መኑ =
3) መጠነ =
4) በይነ =
5) ብነ =
6) ንሕነ =
7) አምጣነ =
8) አነ =
9) ዐይነ =
10)እንበይነ =
11)መሐና =
12)ምዕስብና =
13)ቅኔ =
14)ብለኔ =
15)ጌና =
16)አሐቴኔ =
17)ሕፅን =
18)ሕርትምና =
19)መካን(አጥብቅ) =
20)መካን =
21)ሚጣን =
22)ሰብአ ዐይን =
23)ስጒን =
24)ስን =
25)ስፍን =
26)ረባን =
27)ተወን =
28)ቱገን =
29)ናይን =
30)ናይን =
31)አላቲኖን ሰው=
32)አሶርዮን =
33)ከሙን =
34)ከሚን =
35)ዛሕን =
36)ደርከኖ =
37)ገሪዛን =
38)ጠሊሳን =
39)ጸደና=

3. ዘርእ ቃላት

ዘርእ ቃላት ማለት ማለት ክግሥ የሚወጡ ቀላት ናቸው። የግሡን ሐሳብ ተከትለው ቅጥል ፣ ስም ይሆናሉ። እነዚህም እነደሚከተለው ይቀርባሉ።

3.1. ባዕድነት ያለቸው ቃላት

መስቀል = መስቀያ መቅደስ = መቀደሻ መባእ = መግቢያ

ሙፃእ = መውጫ
ምስካብ = መተኛ
ምቅታል = መግደያ
ምሕዋር = መንገድ
ምስዓል = መለመኛ/መጸለያ
ምንዳድ = ማንደጃ
ምስጋድ = መስገጃ
ማኅደር = ማደሪያ

3.2. ቅጽል የሚሆኑ ቃላት

ለባዊ/ለባዊት = አስተዋይ
ለባሲ/ለባሲት = ለባሽ
ሌዋዊ/ሌዋዊት = ጠምጣሚ
ልዑል/ልዕልት = ከፍ ያለች
ሕኑጽ/ሕንጽት = የተሠራ/ች
ሕያው/ሕያውት = የኖረ/ች
ሐራሲ/ሐራሲት = አራሽ
ሐናጺ/ሐናጺት = አናጢ
ሐዛሊ/ሐዛሊት = አዛይ
ሐያሲ/ሐያሲት = ነጋፊ/ተቺ
መሀሪ/መሀሪት = አስተማሪ
መሓሪ/መሐሪት = ይቅር ባይ
መምክር/መምክርት = መካሪ
መራሒ/መራሒት = መሪ
መሴስይ/መሴስይት = መጋቢ
መቀድስ/መቀድስት = አመስጋኝ
መቅትል/መቅልት = ገዳይ
ምኑን/ምንንት = የተናቀ/ች
መካሪ/መካሪት = መካሪ
መዋዒ/መዋዒት = አሸናፊ
መጣዊ/መጣዊት = ሰጭ
መጋቢ/መጋቢት = አስተዳዳሪ
መጻኢ/መጻኢት = መጭ
መዘምር/መዘምርት = ዘማሪ
መጸብሕ/መጸብሕት = ወጠሠሪ
መደንግጽ/መደንግጺት = አስደንጋጭ
መተንብል/መተንብልት = ጸሎተኛ
መተርጉም/መተርጉምት = ተርጓሚ
መዘክር/መዘክርት = አስተዋሽ
መፍርሕ/መፍርሕት = አስፈሪ
መበይን/መበይንት = ፈራጅ
መአንዝር/መአንዝርት = ዘፋኝ
መዜንው/መዜንውት = ወሬ ነጋሪ
መናዝዝ/መናዝዝት = አረጋጊ
መአብስ/መአብስት = የበደለ/ች
መጥምቅ/መጥምቅት = አጥማቂ
ሙሱን/ሙስንት = የጠፋች
ምንዱብ/ምንድብት = የተቸገረ/ች
ምሁር/ምህርት = የተማረ/ች
ምጥው/ምጥውት = የተሰጠ/ች
ሠያሚ/ሠያሚት = ሿሚ
ሥርግው/ሥርጉት = የተሸላለመ/ች
ምሉእ/ምልእት = የተመላ/ች
ስቁል/ስቅልት = የተሰቀለ/ች

ሰንቃዊ/ሰንቃዊት = ደርዳሪ/ት

ሰያጢ/ሰያጢት = ሻጭ

ሰባኪ/ሰባኪት = አስተማሪ

ሰላሊ/ሰአሊት = ለማኝ

ሰዋቂ/ሰዋቂት = ደጋፊ/ት

ሰፋኒ/ሰፋኒት = ገዥ

ስቡሕ/ሰብሕት = የተመሰገነ/ች

ስኩር/ስክርት = የሰከረ/ች

ስኩብ/ስክብት = የተኛ/ች

ስኩይ/ስክይት = የተከሰሰ

ረዋፂ/ረዋፂት = ሯጭ

ረድእ/ረድእት = ረዳት

ቀታሊ/ቀታሊት = ገዳይ

ቀዳሒ/ቀዳሂት = ቀጅ

ቀዳሲ/ቀዳሲት = አመስጋኝ

ቅውም/ቅውምት = የቆመ/ች

ቡሩክ/ቡርክት = የተባረከ/ች

ቤዛዊ/ቤዛዊት = አዳኝ

ብሩህ/ብርህት = የበራ/ች

ብዑዕ/ብፅዕት = የበቃ/ች

ተመናዪ/ተመናዪት = ምኞተኛ

ተአጋሚ/ተአጋሚት = ታጋሽ

ተአጋሊ/ተአጋሊት = ቀማኛ

ተወላዲ/ወላዲት = ተወላጅ

ተዋናዪ/ተዋናዪት = ተጫዋች

ተአዛዚ = ታዛዥ

ነጋሪ/ነጋሪት = የሚነግር

ነጋዲ/ነጋዲት = ነጋዴ

ነሣኢ/ነሣኢት = ያዥ

ጎሣሚ/ጎሣሚት = ፈላጊ/ተመራማሪ

ጎያሲ//ጎያሲት = የተሸለ/ች

ነጻሪ/ነጻሪት = ተመልካች

ነጋሚ/ጋሚት = ነጋሽ

ጎዙን/ጎዝንት = ያዘነ/ች

አስተጋባኢ/አስተጋባኢት = ሰብሳቢ

አብሣሪ/አብሣሪት = የምሥራች ነጋሪ

አጎዚ/አጎዚት = ያዥ/ጀማሪ

ወፃኢ/ወፃኢት = ወጭ

ዘባጢ/ዘባጢት = መቺ

ዘፋኒ/ዘፋኒት = ዘፋኝ

ዜናዊ/ዜናዊት = ወሬ ነጋሪ

ዘማሪ/ዘማሪት = ዘማሪ

ገባሪ/ገባሪት = ሠሪ

ክቡር/ክብርት = የከበረ/ች

አእኪቲ/አእኪቲት = አመስጋኝ

እጉዝ/እጎዝት = የያዘ/ች

ወላዲ/ወላዲት = ወላጅ

ወዓሊ/ወዓሊት = ሎሌ

ውዱስ/ውድስት = የተመሰገነ/ች

ዐቃቢ/ዐቃቢት = ጠባቂ

ገያሚ/ገያሚት = ገስጋሽ

ጠዓሚ/ጠዓሚት = ቀማሽ

ጸባሒ/ጸባሒት = ወጥ ሠሪ

ጸዋሚ/ጸዋሚት = ጧሚ/ጿሚ

ጸሓፊ/ጸሓፊት = ጣፊ/ጻፊ

ፈዋሲ/ፈዋሲት = ፈዋሽ

ፍትው/ፍትውት = የተወደደ/ች

3. 3. ከሀ-ፐ የተመረጡ ነጠላ ግሦች

ሀ/ሐ

ለቅሐ = አበደረ

ሎሀ = ጻፈ

መልሐ = መዘዘ

ሰብሐ = አመሰገነ

ሰፍሐ = ዘረጋ

ቀምሐ = አፈራ

ቀድሐ = ቀዳ

ቄሐ = ቀላ

በዝነ = በዛ

በጽሐ = ደረሰ

ተመክሐ = ተመካ

ተሞጥሐ = ተጎናጸፈ

ተየውሀ = ገር ሆነ/ተሞኘ

ተፈሥሐ = ደስ ተሰኘ

ነስሐ = ተጸጸተ

ነግሀ = ነጋ

ኖኀ = ረዘመ

አምኀ = እጅ ነሣ

ከርሐ = ግድ አለ

ከልሐ = ጮኸ

ዘብሐ = አረደ

ጠብሐ = አረደ

ጸርሐ = ጮኸ

ጸንሐ = ቆየ

ፈትሐ = ፈረ

ለ

ሐመለ = ለቀመ

ከለለ = አመሰገነ

መሐለ = ማለ

መሰለ = መሰለ

መሰለ = ምስል ሠራ

ሠዐለ = ሣለ

ሰቀለ = ሰቀለ

ሰብለ = ዘረዘረ

ሰአለ = ለመነ

ሰከለ = አፈራ

ቀብለ = ጎደለ

ቀተለ = ገደለ

በቈለ = በቀለ

በጠለ = ጠፋ

ብዕለ = ከበረ/ባለ ሀብት ሆነ

ተሰአለ = ተጠያየቀ

ተቀጸለ = ተቀዳጀ

ተበቀለ = ቂም ያዘ

ተወከለ = ተማነ

ጎዘለ = አዘለ

ጎየለ = በረታ

አከለ = በቃ

አዘለ = በረታ

ከለለ = ጋረደ

ከፈለ = ከፈለ

ወዐለ = ዋለ

ጠለ = ለመለመ

ጠበለለ = ጠቀለለ

ፈተለ = ፈተለ

ዐደለ = በራ

ፈደለ = ጻፈ

መ

ለገመ = ለገመ

ሐመመ = ተመቀኘ

ተርገመ = ተረገመ

ልሕመ = ላመ

ሐረመ = ተወ

ተሳለመ = ተፈቃቀረ

ሐለመ = አለመ

ሐሰመ = ከፋ

ሰብሐ = መሰገነ

ሐመ = ታመመ

ተቃወመ = ተከራከረ

ሜመ = ሾመ

አነመ = ሠራ

ደክተመ = ድሀ አደግ ሆነ

ረገመ = ረገመ

ከርመ = ከረመ

ደገመ = ደገመ

ሰአመ = ሳመ

ቀደመ = ቀደመ

ጠአመ = ቀመሰ

አርመመ = ዝም አለ

ዐቀመ = ለካ/ወሰነ

ጸልመ = ጠቆረ/ጨለመ

አስተሐመመ = አዘጋጀ

ዘንመ = ዘነበ

ጸመ = ጦመ

አቀመ = አቆመ

ረ

መሀረ = አስተማረ

ነገረ = ነገረ

አጥጎረ = ጠመቀ

መሐረ = ይቅር አለ/ራራ

ጎደረ = አደረ

ከብረ = ከበረ

መረ = መረረ

ጎብረ = አንድ ሆነ

ወገረ = ጣሸ/ዕጣን አሳረገ

መከረ = መከረ

ተዝጎረ = ኮራ

ወፈረ = ተሰማራ

መተረ = ቆረጠ

ተገበረ = አረሰ

ያረ = ታወረ

መዝበረ = ፈረሰ

ነበረ = ነበረ

ዘመረ = አመሰገነ

ሠዐረ = ሻረ

አሠረ = አሠረ

ደመረ = ጨመረ

ሠወረ = ሸሸገ

አቈረ = ቋጠረ

ደጎረ = አጨ

ሰክረ = ሰከረ

አንከረ = አደነቀ

ፈከረ = ተረገመ

ባሕረረ = ብርግግ ብርግግ አለ

አእመረ = ዐወቀ

ፈጠረ = ፈጠረ/ወደደ

ሠ/ሰ

ለብሰ = ለበሰ

ለቀሰ = አለቀሰ

ሐረሰ = አረሰ/አዋለደ

ሐንከሰ = አነከሰ

ሐደሰ = አዲስ አደረገ

ሔሰ = ነቀፈ

መርሰሰ = ዳሰሰ

ሜሰ = አደሰ

ሰንኰረሰ = አስተማረ

ቀደሰ = አመሰገነ

ተሞገሰ = ባለሟል ሆነ

ነፍሰ = ነፈሰ

ኀንሰ = አነሰ

ኀመሰ = አምስት አደረገ

ኀሠሠ = ፈለገ/መረመረ

ኀየሰ = ተሻለ

አጽሐሰ = አሸበሸበ

ተከውሰ = ተነቃነቀ

አበሰ = በደለ

ከበሰ = ጠመጠመ

ወቀሰ = ወቀሰ/ተካሰሰ

ወደሰ = አመሰገነ

ወረሰ = ወረሰ

ደምሰሰ = ደመሰሰ/አጠፋ

ደረሰ = ደረሰ

ደቀሰ = ተኛ

የብሰ = ደረቀ

ጌሠ = ገሠሠ

ፈሰሰ = ተሰደደ

ቀ

ሀነቀ = አነቀ

ሐልቀ = አለቀ

ሌቀ = አለቃ ሆነ

ልህቀ = አደገ

ርኀቀ = ራቀ

ሞቀ = ሞቀ

ሠረቀ = ወጣ

ሰሐቀ = ሳቀ

ሰረቀ = ሰረቀ

ሰነቀ = ስንቅ ያዘ

ሰጠቀ = ሰነጠቀ

በረቀ = ብልጭ አለ

ተላጸቀ = አንድ ሆነ

አልጸቀ = ደረሰ

አንፀብረቀ = አፀባረቀ

አድለቅለቀ = አነዋወጠ

አጠቀ = ታጠቀ

ወሰቀ = ሸመቀ

ዖቀ = ዐወቀ

ጠለቀ = ጥልቅ አደረ

በ

ልህበ = ሞቀ

ሐሰበ = ቆጠረ

ሐንበበ = አፈራ

ሐጸበ = አጠበ

መገበ = ሾመ

ሜበ = ሸበተ

ሰረበ = ማገ

ረበበ = ዘረጋ

ሰከበ = ተኛ

ረኀበ = ሰፋ

ረከበ = አገኘ

ርህበ = ተራበ

ረጥበ ረጠበ

ቀርበ = ቀርበ

ቀጸበ = ጠቀሰ

ቄረበ = ቆረበ

ተመንደበ = ተቸገረ

ነሐበ = ሠራ

ነበበ = ተናገረ

አመክአበ = እጥፍ ድርብ አደረገ

አሰበ = ደመወዝ ሰጠ

አተበ = ባረከ

አንበበ = አነበበ

አንጠብጠበ = አንጠባጠበ

አቀበ = ጠበቀ

አውሰበ = አገባ/ሚስት

አጽሐበ = አስጨነቀ

ከበበ = ሾመ

ወሀበ = ሰጠ

ዐርበ = ገባ

ዐፀበ = አስጨነቀ

ዘረበ = ሰደበ

ዘገበ = ሰበሰበ

የበበ = ዕልልል አለ

ጠቀበ = ሰፋ

ጠበ/ጠበበ = ብልሃተኛ ሆነ

ጸወበ = ጨለጠ

ተ

ለተ = ድዳ ሆነ

መመተ = አፈገፈገ

ሞተ = ሞተ/ተለየ

ሜረተ = ሸመተ

ሰንበተ = አከበረ

ሰክተተ = ጣደ

በነተ = ገበረ

ብሕተ = ሰለጠነ

በአተ = ገባ

ቤተ = አደረ

ተአተተ = ሸሸ

ቀነተ = ታጠቀ

ተትሕተ = ተዋረደ/ዝቅ አለ

ነሰተ = አፈረሰ

ነቆተ = ሠራ/የሥዕል ቤት

ጎተተ = መረመረ

አመተ = ከነዳ

አመአተ = መቶ አደረገ

አስተተ = አቃለለ

አእተተ = አስወገደ

አእኰተ = አመሰገነ

አገተ = ከበበ

ከፀተ = ሸፈነ

ነሠተ = አፈረሰ

ከሠተ = ገለጠ

ገዐተ = አገነፋ

ጸለተ = ጋገረ

ፈተተ = ቄረሰ

ፈየተ = ቀማ

ጎ

መንዝጎ = ተደላደለ/ተቀማጠለ

በዝጎ = በዛ

ነዝጎ = ረጨ

ኖጎ = ረዘመ

አምጎ = እጀ ነሣ

አይጎ = አጠፋ

ነ

ሀይመነ = ታመነ

ለሰነ = ተናገረ

ለጠነ = አመሰገነ

ሐበነ = ጠመጠመ

ሐፈነ = ዘገነ

ሐፀነ = አሳደገ

መሐነ = እጅ መንሻ ሰጠ

መነነ = ናቀ

መዘነ = መዘነ/ለካ

መጠነ = ለካ

ረሰነ = ጋለ

ረበነ = አስተማረ

ረጠነ = መድኃኒት አደረገ

ሰሀነ = ሞቀ

ሰመነ = ስምንት አደረገ

ሰሰነ = ትርፍርፍ አለ

ቀነነ = ቀኖና ያዘ

ቀጥነ = ቀጠነ

በየነ = ፈረደ

ባሕነነ = ባከነ

ተሰአነ = ተጫማ

ተቃረነ = ተጣላ

ተንተነ = ተፍገመገመ

ተኳነነ = ተዋቀሰ

ተዐየነ = ተከታተመ

አ

ለክአ ቸነከረ

መልአ መላ

መምአ ተሸበረ

መጽአ መጣ

ሦአ = አረደ/ሠዋ

ቀጽአ = ቀጣ

በጽአ = ተሳለ

ቦአ = ገባ

ተማልአ = እግር መንገድ ሄደ

ተምአ = ተቆጣ

ተሰብአ = ሰው ሆነ

ከ

ሆከ = አወከ

ለሐኰ = ፈጠረ

ለአከ = ላከ

መሐከ = ራራ

መለከ = ገዛ

ተፀወነ = ተጠጋ

አመዝገነ = አመሰገነ

አምነ = አመነ

አውየነ = የወይን ጠጅ አደረገ

አጠነ = አጠነ

ኰነነ = ፈረደ

ኮነ = ሆነ

ተንሥአ = ተነሣ

ተጋብአ = ተሰበሰበ

ተዛውአ = ተጫወተ

ተፈግዐ = ደስ ተሰኘ

ነሥአ = ያዘ/ወሰደ

ጎጥአ = አጣ

ጎድአ = ጸጥ አለ

ጎጥአ = አጣ

አስትአ = ገበረ

አንብዐ = አለቀሰ

አውሥአ = መለሰ

ማህረከ = ማረከ

ሰበከ = አስተማረ

ባረከ = አመሰገነ/መረቀ

ኄከ = አኘከ/አላመጠ

ነሰከ = ነከሰ

ዘፈነ = ዘፈነ

ደመነ = ጠቆረ

ዴገነ = ተከተለ

ድኅነ = ዳነ

ገመነ = ረከሰ

ፈተነ = ፈተነ

ኰርአ = መታ

ወድአ = ፈጸመ

ወውአ = ደነፋ

ወግአ = ወጋ

ወፅአ = ወጣ

ዘርአ = ዘራ

ገብአ = ተመለሰ

ገፍትአ = ገለበጠ

ገፍአ = ገፋ

ጐጕአ = ቸኮለ

ጸልአ = ጠላ

ነክነከ = ወዘወዘ

አምለከ = አመለከ

አስመከ = ተጠጋ

አስተብረከ = ሰገደ/አሰገደ

አውከከ = አጐደለ

ወሀከ = አነሣሣ

ወሰከ = ጨመረ

ደረከ = ጸና/ከፋ

ወ

ሀለወ = ኖረ

ሀለወ = ጠበቀ

ሰበወ = አስተዋለ

ለውለወ = ምላሱን አውለበለበ

ሐረወ = በሳ

ሐሰወ = ዋሸ

ሐይወ = ዳነ

ሐፈወ = ወዛ/ላበት አወጣ

መሐወ = አሸ

መስወ = ቀለጠ

መንሰወ = ጠፋ

መጠወ = ሰጠ

መጽለወ = ጠወለገ

ምህወ = ቀለጠ

ሠረወ = ነቀለ

ሰንቀወ = መታ/መሰንቆ መታ

ቀነወ = ቸነከረ

ቀድወ = አማረ

ቤዘወ = አዳነ/ቤዛ ሆነ

ተሐመወ = አማች ሆነ

ዐ

ድጎከ = ዳኸ/ተንቢቸ

ጐነኰ = ከመረ

ፈለከ = ፈጠረ

ተለወ = ተከተለ

ተመርዐወ = ሙሽራ ሆነ

ተሠርገወ ተሸለመ

ተሠገወ = ሥጋ ለበሰ

ተስጥወ = መለሰ

ተሰፈወ = ተስፋ አደረገ/ታመነ

አለወ = ወነጀለ/ሸፈተ

ዐልወ = ተረጎመ/መለሰ

ተሰነአወ = ተስማማ

ተጌረወ = ቸር ሆነ

ተኬነወ = ብልሃተኛ ሆነ

ጎተወ = በራ

ኖለወ = ጠበቀ

ኖተወ = ዋኘ

አስቆቀወ = አለቀሰ

አስተዳለወ = አዘጋጀ

አተወ = ገባ

አርጎነወ = ከፈተ

አንሶሰወ = ተመላለሰ

አንቃዕደወ = አንጋጠጠ

ፈለከ =በከፈለ

አዕለወ = ተረጎመ/ገለበጠ

አውየወ = ጮኸ/ተፍጀጀ

አደወ = ተሻገረ

አድለወ = አደላ

ዐጸወ = ዘጋ

ከአወ = አፈሰሰ

ወልተወ = መከተ

ካዕለወ = ቀጠቀጠ

ወሀበ = ሰጠ

ደለወ = መዘነ

ደንቀወ = ደነቆረ

ጓሕለወ = ሸነገለ

ጠበወ = ጠባ

ጸልሐወ = ሸነገለ

ጸመወ = ደከመ

ጼነወ = ሸተተ

ፈተወ = ወደደ

ፈነወ = ላከ

ሳዕልዐ = ለምባዳ ሆነ

ሞዐ = አሸነፈ

ሠርዐ = ሠራ

ሰምዐ = መሰከረ

ሰብዐ = ሰባት አደረገ

ሳዕስዐ = ቅልጥፍጥፍ አለ

ነቅዐ =መነጨ

ዘንግዐ = ዘነጋ

ጐሥዐ = ተናገረ

ተፈግዐ = ደስ

አንጦልዐ = ጋረደ

ዘ

ሐወዘ = አማረ

መሐዘ = ጎለመሰ

ምዕዘ = ሸተተ

ረገዘ = ወጋ

ጎበዘ = ጋገረ

ተአንበዘ = ልብ አጣ

ነቅዘ = ነቀዘ

ተገዐዘ = ተጣላ/ተከራከረ

ተፈርዘዘ = ተቀማጠለ

ናዘዘ = አጽናና/አረጋጋ

አመንዘዘ =ችክ ምንችክ አለ

አጎዘ = ያዘ/ጀመረ/ቆጠረ

አውገዘ = ለየ

ከረዘ = ሰቀለ

ገነዘ = ገነዘ/ሸፈነ

ገአዘ = ነቀፈ

ግዕዘ = ነፃ ወጣ

የ

ሀከየ = ሰነፈ

ላህየ = ተጫወተ

ላኰየ = ተከራከረ

ላጸየ = ላጨ

ሌለየ = ለየ

ልህየ = ወፃ

ሐለየ = ዘመረ/ዘፈነ

ሐመየ = አማ

ሐመየ = አሠረ

ሐሰየ = አሸ

ሐከየ = ሰነፈ

ሐዐየ = አጨ

መስየ = መሸ

ሠረየ = ይቅር አለ

ሠረየ = መድኃኒት አደረገ

ሠነየ = አማረ

ረሰየ = አደረገ

ረቀየ = ረጨ

ረዐየ = ጠበቀ

ረወየ = ረካ

ርእየ = አየ

ሰመየ = ስም አወጣ

ሰከየ = ከሰሰ

ሴረየ = ቀለም አገባ

ሴሰየ = መገበ

ቄቀየ = ነፈገ

በልየ = አረጀ

በከየ = አለቀሰ

ተሐሥየ = ደስ ተሰኘ

ተሐበየ = ተዋሰ

ተመነየ = ተመኘ

ተመኵሰየ = ሞክሸ ሆነ

ተሰካተየ = ተማማለ

ተባረየ = ተፈራረቀ

ተነበየ = ትንቢት ተናገረ

ተአበየ = ኮራ

ተጋነየ = ተለማመጠ

ነከየ = ነካ

ጎለየ = አሰበ

ጎረየ = መረጠ

አወፈየ = ሰጠ

አብየ = እቢ አለ

ሄጠ = ሸነገለ

ሐብጠ = አበጠ

ሰበጠ = ሰበጠ

መሠጠ = ነጠቀ

ሜጠ = መለሰ

ሠለጠ = ጨረሰ

ሜጠ = ሸጠ

ጸ/ፀ

ለጸለጸ = መዘነ

ሐረጸ = ፈጨ

ሐነጸ = ሠራ

ሐንፈጸ = ጠረጠረ

ሐጸ = ነደፈ

መጸ = ሆምጣጣ ሆነ/እርሾ ሆነ

ሠረፀ = በቀለ

ረገጸ = ረገጠ

ቀብጸ = ተስፋ አጣ

ፈ

ለከፈ = ነካ

ለፈፈ = ጻፈ

ሐደፈ = አስተማረ

ሐደፈ = ቀዘፈ

ቀሠፈ = ገረፈ

ተሐለፈ = ተነጋገረ

ተአቅፈ = ተሰነካከለ

ተስእሎት ሰባቱ

ሶጠ = ጨመረ

ሰፈጠ = አሳተ

ሰጠጠ = ቀደደ

ቀሰጠ = ሰረቀ

ቀበያውበጠ = ቀላወጠ

ቀጥቀጠ = ሰበረ/ቀጠቀጠ

ተመይጠ = ተመለሰ

ቀነጸ = ዘለለ

በቆጸ = ጫረ

ቤጸ = ለየ

ተባረጸ = አንጸባረቀ

ተባየጸ = ጓደኛ ሆነ

ነቅጸ = ነቀዘ

አመጸ = በደለ

አስተሐየጸ = ተመለከተ

አንፈርዐፀ = ዘለለ

ተወክፈ = ተቀበለ

ተዛለፈ = ተከራከረ

ተሳተፈ = አንድ ሆነ

ነገፈ = አራገፈ

ነጠፈ = ኮላ

አዕረፈ = አራገፈ

አዕቀፈ = አሰናከለ

ተሰውጠ = ተመለሰ

ተሣየጠ = ተገበያየ

አምስጠ = አመለጠ

አስፈጠ = አሳተ

አበጠ = አስገደደ/መለሰ

ፈለጠ = ለየ

አዕቀጸ = አሰናከለ

አድመፀ = አሰማ

ደንገጸ = ደነገጠ

ድጎፀ = ዳጥ ሆነ

ገመጸ = ፍርድ አደላ

ገሠፀ = ተቆጣ

ገገጸ = አፈገፈገ

አውቀፈ = አንባር ሠራ

አዝለፈ = አዘወተረ

ወጸፈ = ወነጨፈ

ዘለፈ = ሰደበ

ጸድፈ = ወደቀ

ፈልሰፈ = ብልሃተኛ ሆነ

ኀለፈ = ሄደ/አለፈ

♣ ከዚህ በታች ከ1-3 ለተጻፉት ቁጥሮች ተስማሚውን ቃል መርጠህ/ሽ አስቀምጥ/ጭ

1. የምስጋና ግሦች
   1.
   2.
   3.
   4.
   5.
2. የኀዘን መገለጫ ግሦች
   1.
   2.
   3.
   4.
   5.
3. የሥራ መገለጫ ግሦች
   1.
   2.
   3.
   4.
   5.
   7.
   8.
   9.
   10.

ተስእሎት ስምንቱ

ከዚህ በታች ከ1-25 የተገለጹትን ክፍት ቦታዎች ተገቢውን የግዕዝ ግሥ/አማርኛ ሙላ/ዪ።

1. .....በላ
2. አንብዐ.....
3. መምዐ .....
4. .....ገላ
5. ፈነወ .....
6. .....መዐደ
7. ..... አስመከ
8. ቀበያውበጠ .....
9. ..... ነጠቀ
10. መከረ.....
11. ..... እጅ ነሣ
12. እንግዳ ሆነ.....
13. .....ይቅር አለ
14. ኮራ .....
15. ሐገገ .....
16. አስተማረ.....
17. .....ሐረጸ
18. መሰንቆ መታ.....
19. ቤጸ.....
20. ወፅአ.....
21. ገብአ .....
22. .....ተሣየጠ
23. ጐንደየ .....
24. .....ተመለሰ
25. ሰጠ.....